# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ኅዳር 7/2008 (ኖቬምበር 17/2015)

የፓርቲው ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ ከኅዳር **3 - 5 / 2008** ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ ለትግሉ ወሳኝ የሆኑ የአገራችንና የዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን በስፋትና በጥልቀት መርምሮ ውሳኔዎችን አስተላልፏል።

የሀገራችንን ሁኔታ አስመልክቶ አሁንም አገራችን በአንድ ጠባብ አምባገነን ቡድን (ወያኔ) የበለጠ ተጠፍራ ያለችበት ሁኔታ መሆኑን ፤ እንዲሁም የሕዝብ መብቶች ከምንጊዜውም በላይ ተጨፍልቀው ድምጻቸውን ያሰሙ ብዕራቸውን የመዘዙ ዜጎች እየታሰሩ፤ እየተሰደዱና እየተገደሉ መቀጠላቸውን አጢኗል። ጋዜጠኞች፣ መምህራን፣ ሠራተኞች፣ የሲቪል ማኅበረሰቡና የፖለቲካ ተቃዋሚ ኃይሎች አባላት በሀገሪቱ በነፃ ሊደራጁና በነጻ ሊንቀሳቀሱ የሚችሉበት ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ያከተመለት መሆኑን ተገንዝቧል።

ከስምንት ሚሊዮን በላይ የሚሆን ሕዝባችን በረሃብ እየተቆላ፤ የቤት እንስሳት፤ የቀንድና የጋማ ከብቶች በገፍ እየረገፉ፣ አቅሙ የቻለው ሕዝብም ምግብ ፍለጋ እየተሰደደ ባለበት ሁኔታ ወያኔ የሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ አመዝግቤያለሁ በማለት የሚያሰማው ዲስኩር ለፖለቲካ ፍጆታ የሚቀርብ ባዶ መመጻደቂያ መሆኑን ተረድቷል። ዛሬም በሥራ እጦት፤ በዕቃዎች ዋጋ መናር፣ በሙስና ጣራ መንካት ሕዝባችን የዕለት ኑሮውን መግፋት እየቸገረው በከፍተኛ ስቃይ ውስጥ መሆኑን በምሬት ተገንዝቧል።

ወያኔ ሀገራችንን ማተራመስ አልበቃ ብሎት፣ በጎረቤት ሀገሮች በሱማሌና በደቡብ ሱዳን ጣልቃ በመግባት ትርምስ እየፈጠረ መሆኑንም አጢኗል። በአፍሪካ ቀንድ የሌሎች ተላላኪ ሆኖ መቀጠሉም ተስተውሏል።

በጎሳ ላይ በተመሰረተው በወያኔ አገዛዝና በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ያለው ቅራኔ በጣም ሰፍቶ ሊታረቅ በማይችልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን አጥፊና ዘረኛ ቡድን ማስወገድ እንዲችል፤ ሁለ-ገቡን ትግል ከማፋፋም በቀር ሌላ ምርጫ እንደማይኖር ወስኗል። ትግሉን በአቸናፊነት ለመወጣትና በሀገሪቱ ዘለቄታዊ ሰላምና ዴሞክራሲ ለማስፈን እንዲያስችል የአንድነትና የዴሞክራሲ ኃይላት መተባበር ወሳኝ መሆኑን ፓርቲው አሁንም ከልብ ያምንበታል ። ዕምነቱንም በተግባር ለማሳየት፤ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ ለሁሉም ወገኖች ጥሪ ሲያቀርብ መቆየቱን አስታውሶ፤ ዛሬም እንደወትሮው የአንድነትና የትብብር ጥሪውን አስተላልፏል።

መደበኛ ስብሰባው የፓርቲውን የውስጥ ጉዳይ በሚገባ መርምሮና ገምግሞ፤ ድርጅታዊ ጥንካሬውን ለማጎልበት የሚያስችሉት ውሳኔዎችን አስተላልፏል። ትግሉ በአባላቱና አካላቱ ብሎም በደጋፊዎቹ እንዲሁም ባጠቃላይ በሕዝቡ በይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና እንዲፋፋም የሚያስችሉ መመሪያዎችን ነድፎ ለሚመለከታቸው ክፍሎች አስተላልፏል። ሕዝባዊ ትግሉ ዳር እስኪደርስ ድረስ በሙሉ ቁርጠኝነት አጠናክሮ ለማስቀጠል፤ ኮሚቴው በፓርቲው ጉባኤ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ቃሉን እንደገና አድሶ ስብሰባውን አጠናቋል።

እናቸንፋለን !

EPRP
P.O.BOX 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645

Email ESPIC@aol.com
Website WWW.EPRP.com

EPRP
BP 30022
92276 Bois Colombes cedex
France